**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 4/2013 በተመለከተ ከሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቀረበ ሪፖርትና የውሳኔ ሐሳብ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-**

የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ም/ቤት ጸድቆ መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም ለአምስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ ለሕግ፣ ፍትሕና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶ ሰፊ ውይይቶች ተደርጎበታል። ይህ ረቂቅ አዋጅ ለመጽደቅ በሂደት ላይ የነበረ ሲሆን በመጭው ማክሰኞ ማለትም ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም የተከበው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲያጸድቀው በአጀንዳነት እንደሚቀርብ ታውቋል። ይህ ረቂቅ አዋጅ ሰፊ ሕዝባዊ ውይይትና ምክክር ተደርጎበት እንዲስተካከል በምሁራንና በባለድርሻ አካላት ተደጋጋሚ ምክረ-ሐሳብ ቢቀርብም አከራካሪ ጉዳዮችን ለማስተካከል ፈቃኝነት አልታየም። በመሆኑም ይህ ረቂቅ ሕግ ከምሁራንና ከባለድርሻ አካላት በቀረበው ምክረ-ሐሳብ መሰረት ሳይስተካከል ከፀደቀ በአጠቃላይ በአገራችን አንድነት በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ራስን በራስ የማስተዳደር ሕገ-መንግሥታዊ መብትና በአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ሕልውና ላይ የሚያደረሰው አደጋ በጣም ከፍተኛ ነው። የዚህን ረቂቅ አዋጅ አከራካሪነትና ኢሕገመንግሥታዊነት በሚከተሉት ነጥቦች ለማሳየት እንሞክራለን።

በረቂቅ አዋጁ ላይ የምጠይቃቸው ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች በዋነኛነት የሚመለከተው የረቂቅ አዋጁን አንቀጽ **25(3)** እና **25(4)** ድንጋጌዎችን ነው። የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** **"**የኦሮሚያ ክልል የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በክልሉ የመንግሥት ጥቅም ላይ በሚፈጽሙት ወንጀል ላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።" ይላል። በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደተደነገገው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ የኦሮምያ ክልል የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ወንጀል የፈፀሙ እንደሆነ ለኦሮምያ ክልል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ይሰጣቸዋል። ይህ ጉዳይ በአገራችን ከተዘረጋው የፌደራል ሥርዓት አንጻር የፌደራል የዳኝነት ሥልጣንና ኃላፊነት የሚጋፋ ነው።

## <u>የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** አከራካሪነት ምክንያቶች</u>

**1.** ይህ የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ ከፌደራልና ከክልሎች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ውጪ በተለየ መንገድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውስጥ ለኦሮሚያ ክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ይሰጣቸዋል። ይህ የዳኝነት ሥልጣን ከየትኛው ሕግ የሚመነጭ ነው**?** ሌላው የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን እንደ ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በግለሰቦች የሥራ ኃላፊነትና የሥራ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ሳይሆን ወንጀል በተፈጸመበት ወይም የወንጀል ውጤት በተገኘበት ቦታና ጊዜ ላይ የሚመሰረት ነው። በዚህ አንቀጽ ላይ በዋነኛነት የተጠቀሰውና ትኩረት የተሰጠው ደግሞ የተፈጸመው ወንጀል ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚኖሩ የኦሮምያ ክልል የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመሆናቸው ከወንጀል

የዳኝነት ሥልጣን ድልድል መርህ ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ አላገኘሁትም። ስለሆነም ይህን የወንጀል ሕግ ጽንሰ-ሐሳብና መርህ በዚህ አንቀጽ እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

**2.** የአንቀጹ መንደንገግ አስፈላጊነትና ዓላማ ግልጽ አይደለም። ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚኖሩ የኦሮምያ ክልል የሥራ ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን ወንጀል ለመዳኘት ከሌሎች ክልሎች በተለዪ ሁኔታና በፌደራል ደረጃ ለኦሮምያ ክልል ፍ/ቤቶች ሥልጣን መስጠት ለምን አስፈለገ?

**2.1** አንዳንድ ጊዜ የፍ/ቤቶች የሥራ ቋንቋ እንደ መሰረታዊ ምክንያትና አስፈላጊነት ተደርጎ ሲነሳ ይደመጣል። ነገር ግን በተግባር እየተሰራ ካለው ሥራ አንጻር የፍ/ቤቶች የሥራ ቋንቋ ጉዳይ ደግሞ ፈፅሞ አሳማኝ አይደለም። ምክንያቱም ማነኛውም ሰው በሚገባውና በሚችለው ቋንቋ በፍርድቤቶች የመዳኘትና ፍትሕ የማግኘት ሕገመንግስታዊ መብቱ ነው። በደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶችም እየተሰራበት ይገኛል። ስለዚህ ይህ መብት ለኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች አልፎ ተርፎም ለውጭ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች የሚሰራ ነው። ስለዚህ ቋንቋ እንደምክንያት ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ስለዚህ የዚህ አንቀጽ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ውስጥ መረቀቅ አስገዳጅነትና ግልጽ ዓላማ ምንድን ነው? ቢብራራ..

**2.2** ሌላው እንደምክንያት የሚነሳው ጉዳይ የኦሮሚያ ክልል መሥሪያቤቶች በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ መገኘታቸውና የአዲስ አበባ ከተማ በኦሮምያ ክልል መሐል መገኘት ነው። ነገር ግን በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የኦሮምያ ክልል መሥሪያቤቶች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና የሌሎች ክልሎች መሥሪያቤቶች ይገኛሉ። ሌላው ኒውዚላንድ በደቡብ አፍሪካ፣ ቫቲካን በኢጣሊያ መሐል እንደ አገራት እንደሚገኙት ሁሉ አዲስ አበባም ዙሪያዋን በኦሮሚያ ክልል የምትዋሰን ለፌደራሉ መንግሥት ተጠሪ የሆነች የፌደራሉ መንግሥት ዋና ከተማ መሆኗ እሙን ነው። በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሥልጣን እንዳለው በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ **49(2)** ላይ በግልጽ ተደንግጓል። በመሆኑም የደቡብ አፍሪካ ፍ/ቤቶች ኒውዚላንድ በሚኖሩ የደቡብ አፍሪካ ሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም የኢጣሊያ ፍ/ቤቶች ቫቲካን በሚኖሩ ኢጣሊያውያን ላይ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው አላነበብንም። ስለዚህ የኦሮምያ ክልል የሥራ ኃላፊዎችንና ሰራኞችን የሚመለከት የወንጀል ዳኝነት ሥልጣን በልዩነት ለኦሮምያ ክልል ፍ/ቤቶች ለምን ይሰጣል? አሳማኝ ሕጋዊ አመክንዮው ቢብራራ... ይሁን ቢባል እንኳን ለዓለም አቀፍና ለአህጉር አቀፍ ተቋማት ባለሥልጣናትና ሠራተኞች እንዲሁም ከኦሮምያ ክልል ውጭ ለሆኑ ሌሎች ሁሉም ክልሎች የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው የወንጀል የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ሕግ ልናወጣ ነው? ይህ ካልሆነስ እነዚህ አካላት በየትኞቹ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሊዳኙ ነው? በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(4)** ላይ እንደተደነገገው በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ ለተለያዩ የክልሎች ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ ከሰጠን

በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል የዳኝነት ሥልጣን ግጭቶች አይፈጠሩምን**?** የዳኝነት የሥልጣን ወሰን **(Jurisdiction)** መሰረታዊ መርሆችንስ አይጥስም**?**

**2.3** አንዳንዶች የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 49(5) ድንጋጌን እንደመነሻ ይጠቅሳሉ። ይኸውም "የኦሮሚያ ክልል፣ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሐል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተደዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።" ይላል።

ነገር ግን የዚህ አንቀጽ የድንጋጌ ክፍል በግልፅ እንዳስቀመጠው በአግልግሎት አቅርቦትና በተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀም ረገድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል መካከል ሊኖሩ ስለሚችሉና የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ስለሚጠበቅ ልዩ ጥቅም የሚደነገግ እንጂ ለኦሮሚያ ፍርድቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ለመስጠት መሰረት የሚሆን ድንጋጌ አይደለም። ስለሆነም የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** ሕገ**-**መንግሥታዊ ወይም ሌላ ሕጋዊ መሰረቱ ምንድን ነው**?**

**2.4** ሌላው ተደጋግሞ የሚገለጸው ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት መቀመጫ በመሆኗ ነው የሚለው ነው። የአዲስ አበባ ከተማ የኦሮምያ ክልል መንግሥት መቀመጫ ሆኗች የተባለው ደግሞ በኦሮሚያ ክልል መንግሥት ውሳኔ እንጅ በፌደራሉ ሕገ-መንግሥት መሰረት ብሎም በተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በወጣ አገራዊ አዋጅ መሰረት አይደለም። ይህን መሰል አገራዊ ጉዳዮች በአገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት፣ ከተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀምና አዲስ አበባ ከተማ በኦሮምያ ክልል መሐል የምትገኝ በመሆኑ በሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳችን በሚመለከት የኦሮምያ ክልል የሚኖረው ልዩ ጥቅም በሕግ ገና ሳይወሰን በፌደራል መንግሥት ዋና ከተማና ራስን በራስ የማስተዳደር ሕገ-መንግሥታዊ መብት ባለው የከተማ አስተዳደር ላይ የአንድ ክልል መንግሥት የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ፍ/ቤቶቹ እንዲኖሩት የወንጀል ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ማቅረቡ ኢ-ሕገ-መንግሥታዊ ከመሆኑም በላይ ከተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሥልጣንና ኃላፊነት ወሰን ውጭ ይመስለኛል። ምክንያቱም የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ ሕዝብ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ላይ የመወሰን ሥልጣን ፈጽሞ የለውም። ስለዚህ የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 25(3) ሙሉ በሙሉ እንዲወጣና የኦሮምያ ክልል መንግሥት በራሱ የአስተዳደር ወሰን ውስጥና ሥልጣን መሰረት ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል የሚል እምነት አለኝ። የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትም ባልተሰጠው ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ ረቂቅ አዋጅ ላይ ውሳኔ አሳልፎ ከታሪካዊ ተጠያቂነት እራሱን እንዲያርቅ እጠይቃለሁ።

**3.** ካለይ እንደተገለጸው የሕገ**-**መንግሥቱ አንቀጽ **49(2)** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን እንዳለው ተደንግጓል። ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚኖሩ ዜጎችን ወይም አዲስ አበቤዎችን ከኃላፊነታቸው ወይም ከሥራቸው ጋር በተያያዘ በሚፈጽሙት ወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ፍ/ቤቶች

መሆናቸው ግልጽ ነው፤ ለዓመታትም እየተሰራበት ይገኛል። ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚኖሩ የኦሮምያ ክልል ባለሥልጣናትና ሠራተኞች በሚፈፅሙት ወንጀል የፌደራል ፍ/ቤቶች ለምን የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን አይኖራቸውም? ምክንያቱም በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ ለሌላ ክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ የመስጠትና የፍ/ቤቶችን የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን የማከፋፈል የዚህ የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕገመንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው አይመስለኝም። በመሆኑም የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** ሙሉ በሙሉ ወጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ የኦሮምያ ክልል ባለሥልጣናትና ሠራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ ለሚፈጽሙት ወንጀል አሁን በሥራ ላይ ባለው የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን (Jurisdiction) መሰረት በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በመዳኘት ሊቀጥል ይገባል።

**4.** የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ **55(1)** መሰረት ለፌደራል መንግሥት በተሰጠው ሥልጣን ክልል ሕጎችን እንደሚያወጣ ተደንግጓል። በተጨማሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጹ **55(5)** የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንደሚያወጣ ተደንግጓል። የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዛሬ እንዲያጸድቀው የቀረበለት የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ለማስፈጸም እንዲቻል ነው። በመሆኑም የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሕገ-መንግሥቱ ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ውጪ ሥልጣን ቆርሶ ለየትኛውም የክልል መንግሥት መስጠት የሚችል አይመስለኝም። በሕገመንግሥቱ አንቀጽ **55(5)** በግልጽ እንደተደነገገው በፌደራሉ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የክልል ም/ቤቶች እንጅ የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ፈፅሞ አይደለም።

ስለሆነም የኦሮምያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚኖሩ ባለሥልጣናቴና ሰራተኞቼ ወንጀል ሲሰሩ የምዳኛቸው በራሴ ፍ/ቤቶች ነው ካለ ለምን በራሱ ም/ቤት የራሱ ሕግ አያወጣም? ከሌሎች ክልሎች በተለየ ሁኔታ ለምን የኢ.ፌዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአዋጅ ሕግ እንዲያወጣለት ፈለገ?

**5.** ሌላው ይህ ረቂቅ አዋጅ በክልሎች መካከል የእኩልነት ስሜትን የሚያጠፋና አንዱ ክልል ከሌላኛው ክልል በሥልጣንና ኃላፊነት እንደሚበልጥ አድርጎ የሚያስቀምጥ አዋጅ ይመስላል። ምክንያቱም የሕጎች ሁሉ መሰረትና የበላይ የሆነው ሕገ-መንግሥት ለሁሉም ክልሎች እኩል የሆነ ራስን በራስ የማስተዳደር ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። ነገር ግን የኦሮሚያ ክልል ፍ/ቤቶችን ብቻ ነጥሎ በማውጣት ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ ይህንን የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን መስጠት ከተገቢነት የራቀ ነው። ምክንያቱም የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ **47(4)** ሁሉም ክልሎች እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው ብሎ ደንግጓል። ስለሆነም የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** ይህን ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ አይጥስም ወይ?

**6.** በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር **1234/2013** አንቀጽ **4(8)** እና **4(16)** መሰረት በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ክልል ውስጥ የሚወድቁ ጉዳዮችንና በአዋጅ በተቋቋሙ ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በፌደራል ፍርድቤቶች ሥልጣን ስር እንደሚወድቁ በሚያመልክት መልኩ የተደነገገ በመሆኑ በአዋጅ የሚወጡ ሕጎቻችንም ወጥነት ሊኖራቸው ስለሚገባ በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ባለሥልጣናትና ሠራተኞች የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የመዳኘት የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ፍርድቤቶች ናቸው ሊባል ይገባል፤ የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 25(3) ሊሰረዝ ይገባል እላለሁ።

በአጠቃላይ የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **25(3)** ድንጋጌ ከላይ በተጠቀሱት ሕጋዊ አመክንዮዎች በጣም አወዛጋቢ፣ አከራካሪ፣ ሕጋዊ ዓላማውና አስፈላነቱ ግልጽ ባለመሆኑ ሙሉ በሙሉ ቢወጣ የሚል ምክረ-ሐሳብ የብዙ የሕግ ምሁራንና ባለሙያዎች በመሆኑ የተከበረው ም/ቤት አባላት ይህንን በመደገፍ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታችንን እንወጣ እላለሁ። በተጨማሪም ረቂቅ አዋጁ ለውይይትና ለመጀመሪያ ንባብ የቀረበው በአምስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በመሆኑ  እንደ ስድስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልነታችን ረቂቅ አዋጁ ለንባብ ሳይሰጠን፤ ጥቅል ማብራሪያ ከመስጠት ያለፈ ዝርዝር ጉዳዮች ቀርበውልን እንደ ሕዝብ ተወካይነታችን የሕግ ድጋፍ በግልጽ ሳይደረግልን፤ የፌደሬሽኑ አካል የሆነው የትግራይን ሕዝብ በተከበረው ም/ቤት ሳይወከል ብሎም አገራችን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር በመሆኗ የም/ቤት አባላትና ዜጎች በረቂቅ አዋጁ ላይ በነጻነት ሐሳባቸውን በመግለጽ ሳይከራከሩበት በተለመደው ረቂቅ አዋጅን በምናፀድቅበት መንገድ ይህን ለብዙ ዓመታት የቆየ አዋጅን በአዲስ አዋጅ በመቀየር አዋጁን ማጽደቅ ይህን የተከበረውን ም/ቤት ታሪካዊ ተጠያቂ ያደርገናል ብዬ አምናለሁ። ስለሆነም የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 25(3) እና 25(4) ሙሉ በሙሉ መውጣት አለባቸው እላለሁ።

አመሰግናለሁ**!!**